የሰ/መ/ቁ 106147

ግንቦት 10 ቀን 2007 ዓ.ም

ዳኞች- አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሱልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመስል

አመልካች፡- እሸት ኢንጅነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - ቀረቡ

ተጠሪ - አቶ ፋንታዬ ቢያድግልኝ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የአውሲረሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 4585 ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 3033 መስከረም 5 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ የጉዳት ካሣ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

1. የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ባቀረበው ክስ የአመልካች ሠራተኛ የሆነ ልጃቸው አመልካች  የንፅህና መጠበቂያ ውሃ ባለማቅረቡ ምክንያት፣ሥራ ውሉ፣ አዋሽ ወንዝ ውስጥ ገብቶ ሲታጠብ ስለመሆኑ በሥራ ላይ እያለ ጉዳት ደርሶበታል፡፡ ስለዚህ የአምስት ዓመት ደመወዝ ብር 270,000 /ሁለት መቶ ሰባ ሺ ብር/ ካሣ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ሟች የድርጅቱ ሠራተኛ አይደለም  ሟች ከአመልካች ንዑስ የሥራ ውል ተዋውሎ የሚሠራው ድርጅት ሠራተኛ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪ ከንዑስ የሥራ ተቋራጭ ሠራተኞች ውሃ የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት ተከሳሽ /አመልካች/ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡
2. የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካችና ሟች የሥራ ውል ግንኙነት የላቸውም፡፡ ሆኖም ከንዑስ ተቋራጩ ሠራተኞች ውሃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት አመልካች መሆኑ በውሉ የተገለፀ

በመሆኑ፣ ተከሳሽ ለሟች ከውል የመነጨ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ብሎ ብር 31,000 /ሰላሣ አንድ ሺ ብር/ እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል። አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቧል። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል።

3. አመልካች ጥቅምት 17 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ ሟች የተጠሪ ሠራተኛ አለመሆኑ ተረጋግጧል። የበታች ፍርድ ቤቶች ባልተከራከርንበት እና በማስረጃ ያልተረጋገጠ ጭብጥ በማንሣት፣ አመልካች፣ ውሃ የማቅረብ ግዴታውን አልተወጣም ብለው የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል ተጠሪ የካቲት 11 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ አመልካች በውል የገባውን ውሃ የማቅረብ ግዴታ መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል። አመልካች መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል።
4. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች የተጠሪ ልጅ በአዋሽ ወንዝ ገብቶ ሲታጠብ ለደረሰበት የሞት አደጋ ኃላፊ ነው ተብሎ ካሣ እንድከፍል የተሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል።
5. ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ ክስ ያቀረበው ሟቹ ልጁ የአመልካች ሠራተኛ ነው። በሥራ ላይ እያለ ጉዳት ደርሶበታል በማለት ነው። የተጠሪ ልጅ የአመልካች ሠራተኛ አለመሆኑ ተረጋግጧል። የተጠሪ ልጅ የአመልካች ሠራተኛ ሣይሆን ከአመልካች ንዑስ የሥራ ውል ተዋውሎ የሚሠራው ንዑስ የሥራ ተቋራጭ ድርጅት ሠራተኛ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ መሆኑን ውሣኔው ያሳያል። ይህ ከሆነ ተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 110 እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ አመልካች ካሣ እንድከፍለው ለመጠየቅ የሚችልበት የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ተጠሪ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግ መሠረት በማድረግ የቀረበው የካሣ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ነው።
6. የተጠሪ ልጅ የንዑስ ሥራ ተቋራጭ ሠራተኛ ነው ከተባለ፣ ተጠሪ ክስ ለማቅረብ የሚችለው በንዑስ ሥራ ተቋራጩ ላይ እንጅ በአመልካች ላይ ሊሆን አይችልም። አንድ ሰው በአንድ ጉዳት ኃላፊ የሚሆነው፣ ከሕግ ከውልና ከውል ውጭ ለጉዳቱ ኃላፊ የሚሆንበት ህጋዊ መሠረት ሲኖር ነው። የበታች ፍርድ ቤቶች ለንዑስ ተቋራጩ ሠራተኞች ውሃ የማቅረብ ኃላፊነት ያለበት አመልካች ነው የማለት አመልካች በተጠሪ ልጅ ላይ ለደረሰው ጉዳት ከውል የመነጨ ኃላፊነት እንዳለበት በመግለፅ ወስነዋል። ሆኖም ፍርድ ቤቶቹ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሱት በአመልካች በንዑስ ሥራ ተቋራጩ መካከል የተደረገውን ውል በዝርዝር ሣያዩና፣ ተጠሪ በንዑስ ሥራ ተቋራጩ ላይ የቀረበው ክስ ሣይኖር፣ ንዑስ ሥራ ተቋራጩ ክስ ቀርቦበት አመልካች

ውል ጋር ያደረገውን ውል እንደመከላከያ ባላቀረበበት ሁኔታ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በውል የገባውን ግዴታ ባለመወጣቱና በተጠሪ ልጅ ሞት መካከል፣ ቀጥተኛ የሆነ የምክንያትና የውጤት ግንኙነት ያለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በተጠሪ በኩል ስለመቅረቡ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ አያሳይም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ለተጠሪ ልጅ ሞት ከውል የመነጨ ኃላፊነት አለበት በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ መሠረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

7. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ በተጠሪ ልጅ ላይ የሞት አደጋ የደረሰበት አመልካች ከውል ውጭ ስለሚመጣ ኃላፊነት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2027 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2136 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት፣ መሆኑን የበታች ፍርድ ቤቶች ውሣኔ አያሳይም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች የተጠሪ ልጅ አዋሽ ወንዝ ገብቶ ሲታጠብ ለደረሰበት የሞት አደጋ ከውል ውጭ በኃላፊነት የሚጠየቅበት የሕግ መሠረት የሌለ መሆኑን ተረድተናል፡፡ አመልካች ከሕግ፣ ከውልና ከውል ውጪ የተጠሪ ልጅ አዋሽ_ወንዝ ገብቶ ገላውን ሲታጠብ ለደረሰበት የሞት አደጋ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ምክንያት ሣይኖር፣ የአውሲረሱ ዞን ከፍተኛ ፍረድ ቤትና የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጡት ውሣኔ ከላይ የጠቀስናቸውን ድንጋጌዎች የሚጥስ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአውሲራሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ ካሣ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ግራቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ብ